## **רפורמת הלמידה המשמעותית – פרסום שאלון לדוגמא (70%)**

מבחן של השפה האמהרית

מנהל תחום דעת: ד"ר אנבסה טפרה

כה אב תשע"ה 10.8.2015

| | |
|---|---|
| አስተውል! መልሶችህን በግልጽና በትልልቅ ፊደሎች በእስክሪብቶ ብቻ ጻፍ | שים לב: את התשובות כתוב ברור, בעט (ולא בעיפרון) ובאותיות גדולות |

| | |
|---|---|
| **ክፍል አንድ** (28 ነጥብ)<br>ከታች በክፍል የተማርከው ምንባብ አለ። የተሰጠውን ምንባብ ካነበብክ በኋላ ከ1-7 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ ወይም በአማርኛ መልስ። | **<u>פרק ראשון</u>** (28 נקודות)<br>קרא את הקטע שלפניך, וענה על כל השאלות 1-7 בעברית או באמהרית. |

## <u>የኤሊና የጥንቸል ውድድር</u>

ኤሊ በጣም ቀሰስተኛ ፍጡር ናት። ምክንያቱም ሰውነቷ ድንጋይ በሚመስል ቆዳ የተሸፈነ ስለሆነ ነው። ጥንቸል ደግሞ ፈጣን ናት። በፍጥነት ከመሮጧ የተነሣ በአጭር ርቀት ውሻ እንኳን አባርሮ አይይዛትም።

አንድ ቀን ኤሊ ሣርና ቅጠሉን ከቃረመች በኋላ ትንሽ ዓረፍ ለማለት ወደቤቷ ስትሄድ ጥንቸልን መንገድ ላይ አገኘቻት። ኤሊም እንደልማዷ በጣም ቀስ እያለች ትሄድ ነበር። ጥንቸዋልም ኤሊን "አንቺ ቀርፋፋ ወዴት ትሄጃለሽ?›" አለቻት። ኢሊም ተናደደችና "ለምን ቀርፋፋ ትዬኛለሽ? ከፈለግሽ ነዩ በሩጫ እንወዳደር" አለቻት። ጥንቸልዋም "እሺ ይሁን" በማለት ተስማማች። "

በሩጫው ቦታ ከተስማሙ በኋላም ቀበሮን የውድድሩ ዳኛ አደረጉት። ቀበሮም "አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት" አለና ሩጫው ተጀመረ። ጥንቸልዋም ኤሊን ወዲያው ቀደመቻት። ኤሊ ግን በጣም ወደኋላ ቀረች። ጥንቸልዋም ኤሊን ለመጠበቅ እሣር ላይ ጋደም አለች። በዚህም ጊዜ እንቅልፍ ወሰዳት። ኤሊም ቀስ እያለች በመሄድ እውድድሩ መጨረሻ መስመር ላይ ደረሰች። ተመልካቾችም ለኤሊ ሲያጨበጭቡላት ሰምታ ጥንቸልዋ ከእንቅልፏ ነቃች። በጣምም ተናደደች። መሸነፍዋንም ሰምታ ጥንቸልዋ ከእንቅልፏ ነቃች። በጣምም ተናደደች። መሸነፍዋንም አወቀችና ኤሊን "ሁለተኛ አልሰድብሽም" አለቻት።

| | |
|---|---|
| **ጥያቄዎች** (28 ነጥብ)<br>በምንባቡ መሠረት ከ1-7 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ ወይም በአማርኛ መልስ። (እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ 4 ነጥብ አለው። በጠቅላላ 28 ነጥብ።) | **השאלות** (28 נקודות)<br>ענה על השאלות 1-7 בעברית או באמהרית לפי הקטע. (לכל תשובה נכונה – 4 נקודות; סה"כ – 28 נקודות) |

1. ኤሊ ቀሰስተኛ ፍጡር የሆነችው ለምንድነው?

2. ኤሊዋ ወደቤት የሄደችው ለምንድነው?

3. ጥንቸል ኤሊዋን መንገድ ላይ ስታገኛት ምን አለቻት? ኤሊዋስ መልሳ ምን አለቻት?

4. ጥንቸል እሣር ላይ ለምን ተኛች?

5. ጥንቸሏ ከእንቅልፏ መቼ ነቃች?

6. ጥንቸሏ መሸነፍዋን ስታውቅ ጊዜ ኤሊን ምን አለቻት?

7. ከምንባቡ የተማርከው ነገር ምንድነው?

| | |
|---|---|
| **ክፍል ሁለት** (28 ነጥብ)<br>ከታች በክፍል ያልተማርከው ምንባብ አለ። የተሰጠውን ምንባብ ካነበብክ በኋላ ከ8-14 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ብቻ መልስ። | **פרק שני** (28 נקודות)<br>קרא את הקטע שלפניך (שלא נלמד בכיתה), וענה על כל השאלות 8 – 14 באמהרית בלבד. |

## <u>ቡና በኢትዮጵያ</u>

በዓለም ታዋቂ መጠጥ የሆነው ቡና ተመሳሳይ ስሞች አሉት ካፌ፣ ኮፊ፣ ቃህዋ፣ ካሼ፣ ወዘተ. ናቸው። ነገር ግን ምንጩ በሆነችው ኢትዮጵያ ስሙ "ቡና" ነው:: በእርሻ ጥናት ተመራማሪዎች መሠረት "አረቢካ" የተሰኘው የቡና ዓይነት የተገኘው በከፋ ክፍለ ሀገር "ቡኖ" በሚባል አካባቢ ባሉት ጫካዎች ውስጥ ነው:: በዚህ ምክንያት አረቢካ ቡናን በማግኘትና ለአገልግሎት በማዋል ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ አገር ናት::

ቡና እንዴት እንደተገኘ ብዙ አፈ ታሪኮች ቢኖሩም ታዋቂው ግን የሚከተለው ነው:: አንድ ቀን "ካልዲ" የሚባል በከፋ የሚኖር እረኛ ፍየሎቹ እንቅልፍ አጥተው ሲቅበጠበጡ ያያቸዋል:: በሁለተኛው ቀን የቡና ፍሬ እንደበሉ ዐወቀና ከፍሬዎቹ ለራሱ ወስዶ ሲበላ እሱም ተነቃቃና እንቅልፍ አጣ:: ከዚያም ይህንን ግኝቱን በአካባቢው ለሚኖሩ መነኩሴዎች አስታወቀ:: እነሱም የቡና ፍሬዎቹን ከበሉ በኋላ እንቅልፍ አጡ:: ለብዙ ዘመናት ቡና ተቆልቶ ይበላ ነበር እንጂ ተፈልቶ አይጠጣም ነበር:: አሁንም ቢሆን በከፋና ሲዳማ ክልል በአንዳንድ ቦታዎች ቡናው ተወቅጦ ከቅቤ ጋር በመደባለቅ ይበላል:: ቡና መፈላት የተጀመረው በ13ኛው ክፍለ ዘመን ነው::

ቡና በኢትዮጵያ ቢገኝም እዚያው ተወስኖ አልቀረም:: በመሆኑም በ14ኛው ክፍለ ዘመን ወደ የመን ተወሰደና "ቃህዋ" የሚል ስም አገኘ:: ይህም ምናልባት "ከፋ" የሚለው ቃል ከቋንቋ ቋንቋ ሲዟዟር በጊዜ ብዛት በመለወጡ ይሆናል:: ከዚያም ቡና ከየመን ወደ ኢንዶኔዚያ በ1690፣ ወደ ሕንድ አገር በ1700፣ ወደ ኮሎምቢያ

በ1714፣ ወደ ብራዚል በ1715 ከተዛመተ በኋላ እንደገና ወደ አፍሪካ በመመለስ በ1877 በከፍተኛ ሁኔታ መስፋፋት ጀመረ::

| | |
|---|---|
| **ጥያቄዎች** (28 ነጥብ)<br>በምንባቡ መሠረት ከ8-14 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ ወይም በአማርኛ መልስ። (እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ 4 ነጥብ አለው። በጠቅላላ 28 ነጥብ።) | **השאלות** (28 נקודות)<br>ענה על השאלות 8-14 בעברית או באמהרית לפי הקטע. לכל תשובה נכונה – 4 נקודות;<br>סה"כ – 28 נקודות) |

8. "ቃህዋ" የሚለው የቡና ስም እንዴት ነው የተፈጠረው? ""

9. "አረቢካ" የተሰኘው ቡና የት ነው የተገኘው?

10. ቡና ከየመን ወደ ሌሎች አገሮች ተወስዷል:: የ3 አገሮችንና ቡና ወደእነዚህ አገሮች የተወሰደበትን ዓመት ጥቀስ::

11. አሁንም ቢሆን ቡናን በአንዳንድ ቦታዎች እንዴት ነው የሚጠቀሙት?

12. በዓለም ላይ ቡና የተለያዩ ስሞች አሉት:: ከእነዚህ ስሞች አራቱን ጥቀስ::

13. ቡና በሌሎች ብዙ አገሮች ሌሎች ስሞች ሲኖሩት በኢትዮጵያ ቡና ይባላል:: ይህ በምን ምክንያት የተነሣ ይመስልሃል?

---

---

14. ቡና እንዴት እንደተገኘ በ4 መሥመሮች ብቻ በአጭሩ ተርክ፡፡

---

---

| | |
|---|---|
| **ክፍል ሦስት** - የሰዋስው ጥያቄዎች (24 ነጥብ) ከ15-22 ላሉት ጥያቄዎች 4 ምርጫዎች ተሰጥተዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ክበብ። (እያንዳንዱ ጥያቄ 3 ነጥብ አለው፣ በአጠቃላይ 24 ነጥብ።) | **פרק שלישי** (16 נקודות) ענה על כל השאלות 15-22. בכל שאלה הקף במעגל את האות מסמנת את האפשרות הנכונה, מבין 4 אפשרויות הנתונות. (לכל תשובה נכונה – 3 נקודות; סה"כ – 24 נקודות) |

15. ብሎ ገዛ ካለ ነገረ ብሎ____ ይላል::

ሀ. አናገረ ሐ. ሰማ

ለ. ተናገረ መ. አለ

16. ትጉህ ለሚለው ቃል ተመሳሳዩ ማን ነው?

ሀ. ታታሪ ሐ. ጥግ

ለ. ጉበዝ መ. ሀ እና ለ

17. መጣ ብሎ ሄደ ካለ ራቀ ብሎ____ ይላል::

ሀ. ሸሸ ሐ. ሩቅ ሆነ

ለ. ቀረበ መ. አልራቀም

18. በዘነ ለሚለው ቃል ተመሳሳዩ ማን ነው

ሀ. ሥራ በዛበት ሐ. ሥራ ፈታ

ለ. ሥራ አጣ መ. ለ እና ሐ

19. ሰጠ ብሎ____ ካለ ሄደ ብሎ አካሄድ ይላል::

ሀ. ስጦታ ለ. ሰጪ

ለ. አሰጣጥ መ. አቀባበል

20. ከእነዚህ ቃላት መካከል ሁለት አጠራርና ሁለት ትርጉም ያለው የትኛው ነው

ሀ. ጋራ ሐ. ቤት

ለ. ዋና መ. ጣራ

21. ሰውዬው “አመዱ ቡን አለ” ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. ከሳ　　　　ሐ. ወዙ ጠፋ

ለ. ደነገጠ　　　　መ. ነጣ

22. ሴትዮዋ “አራስ ነብር ነች” ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. አውሬ　　　　ሐ. ረጅም ጥፍር የላት

ለ. በቅርቡ የወለደች　　　　መ. ቶሎ የምትቆጣ

| | |
|---|---|
| **ክፍል አራት** - ምሳሌያዊ አነጋገሮች<br>(5 **ነጥብ**)<br>ከ23-28 ያሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ።<br>(እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ 2 ነጥብ አለው፥ በጠቅላላ 14 ነጥብ) | **<u>פרק רביעי - פתגמים</u>**<br>(5 נקודות)<br>השלם חמש פתגמים 23-28. (לכל השלמה נכונה – שתי נקודות; סה"כ – 14 נקודות) |

23. ________________________________________ ፣ ከምግብ መለየት።

24. ________________________________________ ፣ ከመጻብ ይቆጠራል።

25. በደንባራ በቅሎ፣ ________________________________________።

26. ጅብን ፈርቼ ዛፍ ላይ ብወጣ፣ ________________________________________።

27. ________________________________________ ፣ አንበሳ ያስር።

28. በሬ ሆይ ሣሩን አየህና፣ ________________________________________።

29. ________________________________________ ፣ ምንጭን ያደንቃል።

| | |
|---|---|
| ከ27-28 ያሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ።<br>(እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ 3 ነጥብ አለው፥ በጠቅላላ 6 ነጥብ) | הסבר במהרית את שני הפתגמים 27-28.<br>(לכל השלמה נכונה – שלוש נקודות; סה"כ – 6 נקודות) |

30. ቀስ በቀስ ዕንቁላል በእግሩ ይሄዳል።

________________________________________________________

________________________________________________________

31. ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራለትም።

________________________________________________________

________________________________________________________